# የኮረና ወረርሽኝ በታክስ ከፋዩ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለመቀነስ
# የወጣ የታክስ ዕዳ ምህረት መመሪያ ቁጥር 64/2012

## 1. አውጭው ባለስልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ለኢኮኖሚ ማነቃቂያ ተብሎ የተደረገውን ውዝፍ የታክስ ዕዳ ማቃለያ ውሳኔ ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኮረና ወረርሽኝ በታክስ ከፋዩ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣ የዕዳ ምህረት መመሪያ ቁጥር 64/2012 "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጉም

በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ወይም በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

ሀ/ "ምድብ "ሀ"" ማለት የኢትዮጵያን በጀት ዓመት ተከትለው ዓመታዊ ሂሳባቸውን ለሚዘጉ ታክስ ከፋዮች እስከ 2007 ዓ.ም ፣ የግሪጎሪያን አቆጣጠር ተከትለው ዓመታዊ ሂሳባቸውን ለሚዘጉ ታክስ ከፋዮች እስከ 2014 ያሉትን የግብር ዘመናት የያዘ ምድብ ነው፡፡

ለ/ "ምድብ 'ለ'" ማለት የኢትዮጵያን በጀት ዓመት ተከትለው ዓመታዊ ሂሳባቸውን ለሚዘጉ ታክስ ከፋዮች ከ2008 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም፣ የግሪጎሪያን አቆጣጠር ተከትለው ዓመታዊ ሂሳባቸውን ለሚዘጉ ታክስ ከፋዮች ከ2015 እስከ 2018 ያሉትን አራት የግብር ዘመናት የያዘ ምድብ ነው፡፡

ሐ/ "የመንግስት ውሳኔ" ማለት በኮረና ወረርሽኝ ምክንያት የኢኮኖሚ ጉዳት የደረሰበትን ታክስ ከፋይ እንዲሁም በሌላው የማህበረሰብ ክፍል ላይ እየደረሰ ያለውን የኑሮ ጫና ለመቀነስ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡

መ/ "የታክስ ዕዳ ምህረት" ማለት ማንኛውም በታክስ ሕግ መሠረት የሚጣል ፍሬ ታክስ፣ ወለድና ቅጣት በምህረት ቀሪ እንዲሆን የተሰጠ የመንግስት ውሳኔ ነው፡፡

ሠ/ "የክፍያ ጊዜ" ማለት በመንግስት ውሳኔ መሰረት ፍሬ ታክስን ለመክፍል የተሰጠ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ያለ ጊዜ ነው፡፡

ረ/ "ታክስ" ማለት በምድብ "ሀ" እና በምድብ "ለ" ባሉት ጊዜያት ያለ ፍሬ (ዋና) ታክስ፣ ወለድ ወይም ቅጣት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አንዱን፣ ሁለቱን ወይም ሶስቱን የያዘ ሊሆን ይችላል፡፡

ሰ/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የገቢዎች ሚኒስትር ነው፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

1/ በገቢ ግብር አዋጅ፣በማዕድን ስራ ገቢ ግብር አዋጅ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ተወስኖ ሊከፈል የሚገባን እስከ 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.እስከ 2018) ባሉት የግብር ዘመናት ላይ ያለን የታክስ ዕዳ የሚመለከት ሲሆን፣ የታክስ ባለስልጣኑ በውክልና በሚሰበስበው ታክስ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

2/ በዚህ መመሪያ የተመለከተው የታክስ ዕዳ ምህረት እና ወለድና መቀጫ የማንሳት ውሳኔ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በአገልግሎት፣ በማምረት፣ በወጪ ንግድ፣ በፋይናንስና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ታክስ ከፋዮች ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>በምድብ "ሀ" የሚገኙ የግብር ዘመናት የውዝፍ ዕዳ ቀሪ አደራረግ</u>

5. <u>የውዝፍ የታክስ ዕዳ ቀሪ አደራረግ ሥርዓት</u>

1/ በምድብ "ሀ" በተጠቀሰው ግብር ዘመን በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው ቀሪ ውዝፍ የታክስ ዕዳ መጠን በምህረት ቀሪ ሆኗል፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 የተገለጸው ቢኖርም፣



አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ሀ) ከሚኒስቴሩ መ/ቤት ውጭ ላሉ አካላት የታክስ አቤቱታ ለማቅረብ ክፍያ የከፈለ እና/ወይም፣

ለ) በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ የሚታየውን የታክስ ዕዳ መጠን ይህ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የከፈለ ታክስ ከፋይ፣ ሌላ ተጨማሪ ክፍያ ሳያስፈልግ የከፈለው በቂ ሆኖ ቀሪው የታክስ ዕዳ በምህረት ቀሪ ይሆናል፡

3/ ከምድብ "ሀ" ውስጥ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት፣በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት የታክስ ክርክር ያለው ታክስ ከፋይ በክርክሩ ለመቀጠል የሚፈልግ ስለመሆኑ ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ካላመለከተ ይህን ውሳኔ እንደተቀበለው በመውሰድ እንደ ሁኔታው የዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) ወይም (2) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (3) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰውና ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው በመታየት ላይ ያለ ከሆነ ክርክሩ የሚቋረጥ ሲሆን የጉዳዩን መቋረጥ ጽህፈት ቤቱ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

5/ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ላይ የታክስ ባለሥልጣኑ ውሳኔውን በመቃወም አቤቱታ ያቀረበ ከሆነ የታክስ ባለስልጣኑ ያቀረበውን የታክስ ክርክር የተወ ስለመሆኑ ጉዳዩ ለተያዘበት አካል እና ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (5) የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ በፍርድ ውሳኔ መሠረት የግብሩ መጠን የተሻሻለ ከሆነና ይህ የተሻሻለው መጠን ግብር ከፋዩ ካስያዘው ገንዘብ ያነሰ ከሆነ ልዩነቱ ለታክስ ከፋዩ ይመለሳል፡፡

7/ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት በተወሰነው ውሳኔ ላይ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ባለስልጣኑ ቅሬታ ቀርቦ በመታየት ላይ ባሉ ጉዳዮች ለየግብር ዘመኑ ለመጨረሻ ጊዜ በቅሬታው ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት የተሰጠው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የውዝፍ ዕዳ መጠን ተደርጎ በውሳኔው መሠረት የሚፈለገው የታክስ ዕዳ ቀሪ ይደረጋል፡፡

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

8/ ታክስ ከፋዩ በታክስ አስተዳደር ሕግ መሰረት የታክስ ቅሬታውን የሚያቀርብ መሆኑን ካልገለጸ በስተቀር መንግስት በሰጠው ውሳኔ መሰረት በምድብ "ሀ" ውስጥ ያለ የታክስ ዕዳ ቀሪ ስለመደረጉ ለታክስ ከፋዩ የጽሁፍ ማረጋገጫ በታክስ ባለስልጣኑ ይሰጣል፡፡

9/ መንግስት በሰጠው ውሳኔ መሠረት ለመስተናገድ የማይፈልግና በታክስ አስተዳደር ሕግ መሰረት ቅሬታ የማቅረብ ሂደቱን መከተል የሚፈልግ ታክስ ከፋይ ቅሬታው ቀርቦ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት የተሻሻለ ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በታክስ ባለስልጣኑ የሚሰጠው ሲሆን ቀጣይ ሂደቱም የታክስ ሕጉን ተከትሎ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (3) እና (6) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት፣ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ በውሳኔው መሰረት እንዲስተካከል የታክስ ውሳኔውን ለወሰነው ለታክስ ባለስልጣኑ የስራ ክፍል የተመለሰ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ወደ ቀጣይ የቅሬታ ደረጃ ይግባኝ የሚጠይቅ ካልሆነ በስተቀር ውሳኔ ማስተካከሉ ይቋረጣል፡፡

11/ በምድብ "ሀ" ውስጥ በሚገኝ የግብር ዘመን የታክስ ዕዳ ኖሮበት በክፍያ ስምምነት ላይ ያለ ታክስ ከፋይ የመንግስት ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሳይከፈል በቀሪነት የሚታየው የታክስ ዕዳ በታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልግ ቀሪ ይደረጋል፡፡

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (6) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በምድብ "ሀ" ውስጥ ያለን የግብር ዘመን የሚመለከት ሆኖ በተለያየ ምክንያት ማለትም በታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት፣ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ለፍ/ቤት ይግባኝ ለማቅረብ የተከፈለ ክፍያ፣ ቅድመ ግብር ክፍያ፣ በትርፍ የተከፈለ ታክስ ወይም ሌላ ገቢ ግብርን የተመለከተ ክፍያ ተመላሽ አይደረግም፤ ለሌላ የግብር ዘመን ዕዳም ማካካሻ አይውልም፡፡

13/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት ምህረት ከተደረገው የታክስ ዕዳ መጠን በላይ ያለ የምድብ "ሀ" የታክስ ዕዳ ለገንዘብ ሚኒስቴር እየቀረበ በምህረት ቀሪ ይደረጋል፡

6. <u>በዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብትና ንብረት</u>

1/ በምድብ "ሀ" ውስጥ በሚገኝ የግብር ዘመን ታክስ ተወስኖ መከፈል ባለበት ጊዜ ባለመከፈሉ ምክንያት ለታክስ ዕዳው ማካካሻ ይሆን ዘንድ የተያዘ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት ለባለሀብቱ ተመላሽ የሚደረገው የግብር ዕዳው የሚፈለግበት ድርጅት በኢኮኖሚው ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

2/ በኢኮኖሚው ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርበው ማስረጃ በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

3/ በኢኮኖሚው ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ላለ ድርጅት የተያዘው ንብረት ሊመለስ የሚችለው ከ2008 ጀምሮ የሚፈለግ ዕዳ የሌለበት ሲሆን ብቻ ነው፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተያዘ ንብረት ተመላሽ የሚደረግለት ታክስ ከፋይ ንብረቱን እንዲረከብ በማስታወቂያ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ ንብረቱን ካልተረከበ ንብረቱ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

5/ በምድብ "ሀ" ውስጥ ያለ በመንቀሳቀስ ላይ ድርጅት ከሌሎች ባለገንዘቦች በሚፈለግ ዕዳ ምክንያት ንብረቱ በተጨማሪነት በፍርድ ቤት የታገደ ከሆነ ንብረቱ ሊመለስ የሚችለው ታክስ ከፋዩ በፍርድ ቤት ስለሌሎች ዕዳዎች ውሳኔ አሰጥቶ ሲመጣ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል 3

## በምድብ "ለ" የሚገኙ የግብር ዘመናት የውዝፍ ዕዳ ቀሪ አደራረግ

### 7. የውዝፍ የታክስ ዕዳ ቀሪ አደራረግ ሥርዓት

1/ በምድብ "ለ" ውስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን ታክስ ተወስኖ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በዚህ አንቀጽ በሌሎች ንዑስ አንቀጾች የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚፈለግበት ውዝፍ የታክስ ዕዳ ወለድ እና/ወይም መቀጫ ብቻ ከሆነ ዕዳው ቀሪ ተደርጓል፡፡

2/ የታክስ ዕዳ ምህረትን የሚመለከተው የመንግስት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የታክስ ኦዲት ተደርጎ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በምድብ "ለ" ውስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን ዋና (ፍሬ) ታክስ፣ ወለድ ወይም መቀጫ ያለበት ከሆነ ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ መንግስት የታክስ ዕዳን ለማቃለል በሰጠው ውሳኔ ለመጠቀም የመረጠ መሆኑን ለታክስ ባለስልጣኑ ካመለከተና፦

ሀ) በክፍያ ጊዜ ስምምነት መሰረት የሚከፍል ከሆነ የፍሬ ታክሱን 25 በመቶ በቅድሚያ በመክፈል ቀሪውን 75 በመቶ በአንድ ዓመት ውስጥ ለመክፈል የክፍያ ጊዜ ውል ተፈራርሞ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ ወለድና መቀጫው ይነሳል፡፡ በመክፈያ ጊዜ ውስጥ ተጨማሪ ወለድ እና መቀጫ አይታሰብበትም፡፡

አህመድ ሽዴ
ሚኒስትር

ለ) በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬ ታክሱን ከከፈለ፦

1. ከፍሬ ታክሱ መጠን 10 በመቶ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡
2. የፍሬ ታክሱን 90 በመቶ ብቻ ይከፍላል፡፡
3. በታክስ ውሳኔው መሠረት የሚከፈለው ወለድና መቀጫ ቀሪ ይደረጋል፡፡

3/ በመንግስት ውሳኔ መሰረት ለመስተናገድ ያመለከተ ታክስ ከፋይ በደረሰው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት፣ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ ፍርድ ቤት ያቀረበውን የታክስ ክርክር ያቋረጠ ስለመሆኑ ጠቅሶ ለታክስ ባለስልጣኑ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ማመልከት አለበት፡፡ ሆኖም የመቀጫና ወለዱ ዕዳ መነሳቱን የሚገልጽ ማስረጃ ከታክስ ባለስልጣኑ ሊሰጥ የሚችለው ታክስ ከፋዩ ክርክሩን ያቋረጠ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አግባብ ካለው አካል ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

4/ ታክስ ከፋዩ በመንግስት ውሳኔ መሰረት ለመስተናገድ ካመለከተ የታክስ ባለሥልጣኑ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ ያቀረበበትን የታክስ ክርክር የተወ ስለመሆኑ ጉዳዩ ለተያዘበት አካል እና ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ በፍርድ ውሳኔ መሠረት የግብሩ መጠን የተሻሻለ ከሆነና ይህ የተሻሻለው መጠን ግብር ከፋዩ ካስያዘው ገንዘብ ያነሰ ከሆነ ልዩነቱ ለታክስ ከፋዩ ይመለሳል፡፡

6/ መንግስት የታክስ ዕዳን የማቃለል ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት የመክፈያ ጊዜ ስምምነት የገባና በመክፈል ላይ ያለ ታክስ ከፋይ በውሳኔው መሰረት ለመስተናገድ ከተስማማ፦

ሀ) ቀደም ሲል በምድብ "ለ" ውስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን የተከፈለ ወለድና ቅጣትን ሳይጨምር የተከፈለው ጠቅላላ ክፍያ ከፍሬ ታክሱ የበለጠ ከሆነ ባለበት ይጠናቀቃል፡፡

(ለ) ቀሪ የታክስ ዕዳ ካለው ቀደም ሲል የመክፈያ ጊዜ ስምምነት ላይ የነበረው ውል ተሰርዞ ቀሪ ፍሬ ታክሱን 25 በመቶ በቅድሚያ በመክፈል ቀሪውን ታክስ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለመክፈል አዲስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል መፈረም አለበት፡፡

አህመድ ሽዴ
ሚኒስትር

7/ ገቢውን አስታውቆ የከፈለ ሆኖ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ያልደረሰው ታክስ ከፋይ በታክስ ኦዲት መሠረት የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ በመቅረብ በታክስ ዕዳ ማቃለያው የመንግስት ውሣኔ መሰረት መስተናገድ ከፈለገ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) እና (ለ) በተገለጸው መሠረት መስተናገድ ይቻላል፡፡

8/ ገቢውን አስታውቆ ያልከፈለ ታክስ ከፋይ ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ገቢውን ካስታወቀ፡-

ሀ) የሚከፈል ታክስ ባይኖር የሚጠየቀው መቀጫ እና/ወይም ወለድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ቀሪ ይደረጋል፡፡

ለ) የሚከፈል ታክስ ካለ እና ፍሬ ታክሱን ሙሉ በሙሉ ከከፈለ ፍሬ ታክሱ ላይ የሚሰላው ወለድና መቀጫ ቀሪ ይደረጋል፡፡

ሐ) ታክስ ከፋዩ ያስታወቀውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የታክስ ኦዲት ተደርጎ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ 30 ቀናት ውስጥ በመቅረብ በመንግስት ውሣኔ መሰረት መስተናገድ ከፈለገ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) እና (ለ) በተገለጸው መሠረት መስተናገድ ይችላል፡፡

9/ ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የታክስ ዕዳን ለማቃለል በተሰጠው የመንግስት ውሳኔ ለመጠቀም የመረጠ መሆኑን ለታክስ ባለስልጣኑ ካላመለከተ በመንግስት የታክስ ዕዳ የማቃለል ውሣኔ መሰረት መስተናገድ እንዳልፈለገ ተወስዶ መደበኛው የታክስ ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

10/ ታክስ ከፋዩ በመንግስት የታክስ ዕዳ የማቃለል ውሣኔ መሰረት በዚህ ምድብ ውስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስምምነት ገብቶ በስምምነቱ መሰረት በአንድ ዓመት ውስጥ ከፍያውን አጠናቆ ካልከፈለ የታክስ ዕዳ የማቃለል ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት የነበረና ያልተከፈለን ፍሬ ታክስ ወለድና ቅጣት በታክስ ሕጉ መሰረት መክፈል የሚገባው ሲሆን ባልተከፈለው ታክስ ላይ መደበኛው የታክስ አስተዳደር ሕግ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

11/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት ምህረት ከተደረገው የታክስ ዕዳ መጠን በላይ ያለ የምድብ "ለ" የታክስ ዕዳ ለገንዘብ ሚኒስቴር እየቀረበ በምህረት ቀሪ ይደረጋል፡፡

አህመድ ሽዴ
ሚኒስትር

## 8. በዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብትና ንብረት

1/ ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳን ለማቃለል በተሰጠው የመንግስት ውሣኔ መሰረት በምድብ "ለ" ውስጥ የሚገኝን የግብር ዘመን ፍሬ ታክስ በአንዴ ወይም በክፍያ ጊዜ ስምምነት መሰረት ከፍሎ ከጨረሰ የታክስ ባለስልጣኑ በታክስ ዕዳ የተያዘ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለውን ዕግዱን በማንሳት ንብረቱን ለታክስ ከፋዩ ይመልሳል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የታክስ ዕዳውን ከፍሎ የጨረሰ ታክስ ከፋይ ክፍያውን ከፍሎ ካጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ንብረቱን ለመረከብ አመልክቶ የርክክብ ሂደቱን ካልጀመረ ንብረቱ እንደተተወ ቆጥሮ የመንግስት ሀብት ሆኖ ይመዘገባል፡፡

3/ ታክስ ከፋዩ በዚህ ምድብ ውስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን የታክስ ዕዳን ለማቃለል በተሰጠው የመንግስት ውሣኔ የፍሬ ታክሱን 25 በመቶ በቅድሚያ ከፍሎ እስከ አንድ ዓመት የመክፈያ ጊዜ ስምምነት የተፈራረመ ከሆነ የታክስ ባለስልጣኑ ለዕዳ ማካካሻ የያዘውን የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት ታክስ ከፋዩ እንዲሰራበት ለፈቅድ ይችላል፡፡ ታክስ ከፋዩ ዕዳውን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ሲያጠናቅቅ እግዱ ተነስቶ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የሚንቀሳቀስ ንብረትን ታክስ ከፋዩ እንዲሰራበት በታክስ ባለስልጣኑ የሚፈቀደው ባልተከፈለው ታክስ መጠን (ወለድና ቅጣትን ጨምሮ) የባንክ ዋስትና ካስያዘ ነው፡፡

5/ በምድብ "ለ" ውስጥ በሚገኝ የግብር ዘመን ታክስ ተወስኖ መከፈል ባለበት ጊዜ ባለመከፈሉ ምክንያት ለታክስ ዕዳው ማካካሻ ይሆን ዘንድ የተያዘ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት ዕዳው ተከፍሎ ሳይጠናቀቅ ለባለሀብቱ ተመላሽ የሚደረገው የግብር ዕዳው የሚፈለግበት ድርጅት በኢኮኖሚው ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

6/ በኢኮኖሚው ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርበው ማስረጃ በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

## ክፍል 4

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. የአፈጻጸም ስርዓት ስለመዘርጋት

የገቢዎች ሚኒስቴር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይችላል፡፡

10. ተፈጻሚነት የሌለቸው መመሪያዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ለተመለከቱ ውሣኔዎች አፈጻጸም ብቻ ጥቅም ላይ አይውሉም፡፡

1/ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 137/2010 (ከነማሻሻያው)

2/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 142/2011

11. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 28 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ.ም

አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር